# ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

ጌታቸው ኃይሌ

April 25, 2018

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝን ወምበር ስለወሰደ ብዙ ሰዎች የሆነውን ትተው ያልሆነውን እንደሆነ አድርገው የራሳቸውን ምኞትና ፍላጎት ሲተቹ ሰነበቱ። እኔም አንዱ ሆኜ፥ በአንዳንድ የውይይት መድረኮች ላይ የመሰለኝን ገልጫለሁ። ይህ ጽሑፍ የነዚያ ሐሳቦቼ ጥርቅም ነው።

የሆነው የኢሕአዴግ ፓርቲ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የለቀቀውን ሥልጣን የሚተካበት ሰው ፈልጎ ዶክተር ዐቢይ አሕመድን አግኝቶ መተካቱ ነው።

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወምበሩን ሲረከብ ያደረገው ንግግር ተቺዎችን በሁለት ምክንያት አሳስቷል ። አንደኛ፥ ንግግሩን ለመረጠው ለፓርቲው ማድረጉን ትቶ ላልመረጠው ለኢትዮጵያ “ሕዝቦች” አደረገው፤ ሁለተኛ፥ ንግግሩ ያነጻጸረው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስለሆነ፥ ከኢሕአዴግ መሪ እስከ ዛሬ ጎልቶ ያልወጣ ኢትዮጵያዊነትን ስመ አምላክን ከሙሉ አፉ፥ በሙሉ ጆሯችን አስሰማን። ይህን ስንሰማ፥ ኢሕአዴግ መሪ ለወጠ ማለታችንን ትተን፥ “በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ተደረገ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ኦሮሞ የኢትዮጵያ መሪ ሆነ” አልን። ግን ሥልጣኑ የፓርቲው ነው፤ ፓርቲው በአገዛዝ ላይ እስካለ ድረስ መሪውን በፈለገው ጊዜ ቢለውጥ የሥልጣን ሽግግር ተደረገ አያሰኝም። ሁለተኛም፥ የንጉሥነቱን ሥልጣን ሳይቀር ኦሮሞዎች የያዙበት ዘመን እንደነበረ ተረሳ።

ባጭሩ፥ ኢሕአዴግ ችግር ላይ በወደቀበት ሰዓት የሚያድነው ፈለገ። በኢሕአዴግ አስተሳሰብ፥ ጅጅጋ፥ አምቦ፥ ወሊሶ፥ ወልቂጤ እየተሯሯጠ የተነሣበትን እሳት የሚያጠፋ ለእሳት አደጋ ፈጥኖ ደራሽ ዶክተር ዐቢይ አሕመድን አገኘ። ግን እውነት የሆነው ይህ ነው? ለኢሕአዴጎች መዳን ማለት ምን ማለት ነው? ተቃውሞ ረግቦላቸው አገዛዛቸውን መቀጠል ነው ወይስ ሕዝብ ሳይሰቅላቸው ሥልጣን በሰላም ማስረከብ ነው? ሥልጣን በሰላም ማስረከብ የወሰዱት እርምጃ ከሆነ ድንቅ ፖለቲካ ነው። ዘመኑም የሰላም እንጂ የቂም በቀል አይሆንም። ታዲያ ለምን አልመረጡትም?

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚባለውን ክፉን ሐሳብ በማንሣት ልጀምር፤ ወያኔዎች አማራውን እንደሚጠሉ፥ ቢጠፋም እንደሚመኙ፥ የተቻላቸውን ያህል ቍጥሩን እንደቀነሡትም ግልጥ ነው። “እነሱ ካልገዙ፥ ሥልጣኑን ለኦሮሞች አስረክበው፥ ኦሮሞዎች የደረሰባቸውን ጡት ቆረጣ እንዲበቀሉ አድርገው ይሄዳሉ” እንደተባለም ግልጽ ነው። ኦሮሞውን ዶክተር ዐቢይን ሳይመርጡት ሥልጣኑን ከለቀቁለት፥ “ ለሚፈጸመው እልቂት ከደሙ ንጹሕ ነን። የጨረሳችሁ እናንተ የመረጣችሁት ነው” ለማለት ይሆናል።

ዶክተር ዐቢይስ ራሱን እንዴት ነው ያየው? ከአያያዥ ይቀደዳል፤ ከአነጋገር ይፈረዳል እንደሚባለው፥ ከንግግሩ እንደምንገምተው፥ የኢትዮጵያ ታሪክ የእሱና የሁላችንም ታሪክ መሆኑን የተረዳ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ነው። የኮራበት ታሪክ እውነተኛ መሆኑን ማስረጃ ከፈለገ፥ የታሪክ ሰነድ የሚያቀርቡለት

መምህራን አሉት። እንዲህ ያለውን ኩሩ ሰው (ያውም ክርስቲያን የአማራ ልጅ) ፎክሮ የተነሣው የሕዝብን ፍላጎት ለመፈጸም እንጂ የአባቱንና የናቱን ወገኖች ለማጫረስ አይደለም።

በመጀመሪያው ንግግሩ ያተኮረው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ መሆኑ ቀርቶ በኢትዮጵያ “ሕዝቦች” ላይ መሆኑ ያደናግጣል። ግን ስለዚህ ጉዳይ ሁለት ነገሮች በአእምሮየ መጡ፤ አንደኛ፥ በመጀመሪያ ንግግሩ፥ “ከዛሬ ጀምሮ ‘ብሔሮች’፥ ‘ሕዝቦች’ የሚሉትን ቃላት ከፖለቲካ ቋንቋችን ሰርዣቸዋለሁ” ሊል አይችልም። ሁለተኛ፥ “ብሔሮች”፥ “ሕዝቦች” የ “Nations”, “Nationalities” ትርጉሞች እስካልሆኑ ድረስ ልንቀበላቸው እንችላለን። በግዕዝና በአማርኛ “ሕዝብ” ብዙ ትርጉም አለው። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ “ወገን፡ ነገድ፤ የተሰበሰበ፡ ብዙ፡ ሰው፤ ጉባኤ፡ ሸንጎ፤ ልቅሶኛ፡ ሰርገኛ፡ ገበያተኛ። ያንዲት አገር፡ ያንዲት፡ ከተማ፡ ወይም፡ ያንድ፡ ብሔር፡ ያንድ፡ መንግሥት ሰው፤ ቋንቋውና፡ ሕጉ፡ አንድ፡ የሆነ፤ ባንድ፡ ሕግ፡ የሚኖር” ይሉታል። ሕዝብ “ሰው” ማለት ሲሆን፥ “እገሌ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት የማይረሳ ንግግር አደረገ” እንላለን።

የተቸገርነው ልጆቹ እነዚህን ቃላት የ“Nations”, “Nationalities”ን ጣጣ ስለጫኑባቸው ነው። ብሔሮችማ በ“Nations”ንም ሆነ በ“Nationalities” ሊተረጐም አይችልም። ብሔር ምድር እንጂ ሕዝብ አይደለም። እንዲህ ከሆነ፥ ነገዶችን ሕዝብ ብንላቸው ጉዳቱ አይታየኝም። አንድነታችንን ዓላማችን አድርገን ምሁራዊ ውይይት ብናደርግ አገራችንን ልንጠቅም እንችላለን። ዶክተር ዐቢይም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር ከሆነ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ የኢትዮጵያ ነገዶች መሪ አይደለም። ነገዶችን መሪዎቻቸው ይምሯቸው። ሆኖም፥ ከንግግሩና ከሌላም አጋጣሚ እንደምንረዳው፥ ኦሮሞዎች የኢትዮጵያ ታሪክ የሁላችንም መሆኑን መረዳትና መቀበል ጀምረዋል። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ካገኘቻቸው ድሎች ከየትኛውም የማያንስ ነው።

“ነገዶች ‘ሕዝቦች’ መባልን ይመርጣሉ” የሚለው አስተያየት በጥናት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ነገዶች ምስጢሩን ቢረዱት፥ አጥብቀው ይርቁታል። ምስጢሩ የኢትዮጵያ አኵሪ ታሪክ የአንድ ግፋ ቢል የሁለት ሕዝቦችታሪክ እንጂ የኢትዮጵያውያን ነገዶች ሁሉ ታሪክ አይደለም ማለት ነው። ነገዶች፥ “ሕዝቦች” መባልን ከመረጡ ራሳቸውን ከኢትዮጵያ ታሪክ ማራቆታቸው ነው። የምሁራን አገልግሎት ይኸንን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለመሪዎች በማስረጃ ማቅረብ ነው።

ዶክተር ዐቢይ ኢሕአዴግ ቀብሮት ለነበረው ኢትዮጵያዊነት ሕይወት ስለሰጠው ብዙዎቻችንን አስደስቶናል። አንዳንድ ሰዎች ግን፥ ደርግ የጨረሰን በኢትዮጵያዊነት ስም ስለሆነ፥ ለዚህ ዋጋ እንዳንሰጠው ያስጠነቅቁናል። ግን ይኸን ማስጠንቀቂያ የሚሰጡን ሰዎች ኢሕአዴግ ለኢትዮጵያዊነት ዋጋ በመስጠት ከደርግ ዝቅ ያለ መሆኑን የሚረሱ ይመስለኛል። እንደኛ የሚያስብ መሪ የኛ ሰው ነው። ግን ለሆነው እያመሰገንን ግፊታችንን መቀጠል አለብን።

ስለወያኔዎች አቋም የተለያየ ሐሳብን የጠራው፥ ምርጫው በተካሄደ ጊዜ፥ ዶክተር ዐቢይ ከሕወሓት አባላት አንድም ድምፅ አለማግኘቱ ነው። ምን ማለት ሊሆን ይችላል? ሥልጣኑ በእጃቸው ያለው ወያኔዎች ለሥልጣናቸው የሚያሰጋ ሰው ሲመረጥ ዝም ብለው ተቀበሉት ማለት ይቻላል? ወይስ ወያኔዎች የማይችሉት ግፊት ስለመጣባቸው፥ በክብር ለመሰናበት መዘጋጀታቸው ነው? በአሁኑ ሰዓት ማንም ሰው ቢሆን እየሆነ ያለውን እንጂ የሆነውንና የሚሆነውን ለማወቅ የሚችል የለም። ሌላው የተያያዘ ጥያቄ፥ ወያኔዎች ለውድድሩ እንደተለመደው አንድ ሰው ብቻ አለማቅረባቸው ነው። ሁለት ሦስት ሰዎች ለምርጫ አቅርበው፥ ለኢሕአዴግ አባላት የተያዘባቸውን የመምረጥ መብት ለቀቁላቸው። እነሱም እንደ እስረኞቹ ተፈቱ። የሚፈልጉትን ስለመረጡ፥ ሕወሓት እያነሰ እነሱ እየተለቁ የሄዱ መሰለ።

ዶክተር ዐቢይ ጀግና ከሆነ (ይሆንም ይመስለኛል) በኢሕአዴግ ክልል ውስጥ ጀግንነቱን ሊያሳይ ይችላል። መቸም ኢሕአዴግ እስካለ ድረስ፥ የኢሕአዴግ መሪ ከኢሕአዴግ ክልል ውጪ ይሠራል ብለን አንጠብቅም። “ከሕገ መንግሥታቸው ውስጥ የሚከፋፍለንንና አገሪቱን የሚበታትነውን አንቀጽ 39 እስካልደመሰሰ ድረስ ለውጥ አመጣ አንልም” የሚሉ አሉ። ይኸን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስገድደው የሚቀጥለው የሕዝብ ግፊት ነው። “የኢሕአዴግ ክልል” የምለው የኢሕአዴግን ሕገ መንግሥትን ነው። ኢሕአዴግ የበደለን (1) የሚከፋፍለን ሕገ መንግሥት በማወጁና (2) ያወጀውን ሕገ መንግሥት እየጣሰ በመጨቈን ነው። ዶክተር ዐቢይ የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት በፈቀደለት መሠረት፥ ሕዝቡ በነፃነት እንዲጽፍና እንዲናገር፥ መሰብሰብ ሲፈልግ በነፃ እንዲሰበሰብ፥ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ሲፈልግ መሰለፍ እንዲችል፥ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲያቋቁሙና በነፃ እንዲወዳደሩ የሁሉንም መብት በፖሊስ ማስጠበቅ መብቱ ነው። ይህን የራሱን መብት ማስጠበቅ ካልቻለ የኛን መብት አያስጠብቅም። ግን በሙብቱ ተጠቅሞ፥ ለሕዝብ አገልግሎች ከሰጠ፥ የሚሰጠውን አገልግሎት ከስር ከስሩ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት ለሕዝብ ማስታወቅ ይኖርበታል። ይኸንን ማድረግ ከቻለ ወያኔዎች ጣልቃ መግባታቸውን ለማቆም ይገደዳሉ። ካላቆሙ የሕዝብን ቁጣ ማስነሣት ይሆንባቸዋል። ዶክተር ዐቢይ ወያኔዎች ከእንግዲህ ወዲህ የሕዝብን ቁጣ ካስነሡ መቃብራቸውን መቆፈራቸው መሆኑን ዐውቆ፥ በድፍረት መራመድ ይኖርበታል። ወያኔዎች ከአሁን በፊት ድል ያገኙት ሕዝብ የጠላውን ደርግን ተዋግተው ነው። የእንግዴህ ወዲሁ ጦርነት ግን ከሕዝብ ጋር ስለሚሆን፥ መለስ ዝና-ቢሱ እንዳለው ሕዝብ ያሸንፋል እንጂ አይሸነፍም።

ዋናዎቹ የፖለቲካ ችግሮቻችን ሁለት እንደሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ይመስለኛል። ከላይ እንደተቸሁት፥ አንደኛ፥ ወያኔዎች ሕዝብ ያልጻፈው፥ ሕዝብ ከፋፋይ ሕገ መንግሥት ማወጃቸው፤ ሁለተኛ፥ የራሳቸውን ሕግ እየጣሱ በሕዝብ ላይ መጨማለቃቸው ነው። ሁለተኛውን ችግር ዶክተር ዐቢይ በተሰጠው ሥልጣንና ማንም ሳያስገድደው በሰጠን ተስፋ መሠረት ሊያስወግደው ይችላል። ሁለተኛውን ሲያስወግድልን፥ አንደኛው ዐውቆ ይወገዳል። ማለት፥ ውድድሩን በነፃ የምርጫ ቦርድ፥

በተወዳዳሪዎችና በዓለም-አቀፍ ታዛቢዎች እንዲፈጸም በፖሊስ ኃይል ሲያስፈጽም፥ አሸናፊው ፓርቲ ሥልጣን ይዞ ሕገ

መንግሥቱን ሊያስተካክል ይችላል። በዚህ ጊዜ ከወያኔ ጋር ግብ ግብ ሊገባ፥ ሊሡዋም ይችላል። እንደ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ከመሸሽ፥ ለሀገር መሥዋዕት መሆን ለጀግና አዲስ ነገር አይደለም፤ ስምን ከመቃብር በላይ ያደርጋል። ሕዝብም ዝም አይልም።

ሁለተኛው ችግር የሁላችንም ችግር ነው። መብታችን ይጠበቅ ማለት የሁላችንም ጩኸት ነው። አንደኛው ችግር ግን የሁላችንም ለመሆኑ እርግጠኛ አይደለሁም። አንዳንድ ሰዎች በክልል ከፋፋዩን ሕገ መንግሥት ወድደው፥ የጠሉት መንግሥት በውስጥ አስተዳደራቸው መግባቱን ነው። "ለዚህ ችግር መፍትሔው የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ነው" የሚሉ አሉ። የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ቢቻል ጥሩ ነው፤ ግን አይቻልም፤ መፍትሔም አያስገኝም። መጀመሪያውኑ ኢሕአዴግ ምንም ጫና ቢበዛበት የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም አይፈቅድም። ከፈቀደ እስከዛሬ የገዛው አለ ሕግ መሆኑን ማመን ይሆንበታል። ደግሞስ፥ ከሽግግሩ መንግሥት ውስጥ እነማን ገብተው እነማን ይቀራሉ?

ከሁሉም ለሁሉም የሚያዋጣው ነፃ ምርጫ ማካሄድ ነው። ለኢሕአዴግም የተሻለው መውጫ በር ነፃ ምርጫ ማካሄድና በምርጫ ተሸንፍኩ ብሎ በክብር መሰናበት ነው። ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ ከፈቀዱ ራሱ መፍቀዳቸው ያስከብራቸዋል። ሁለተኛም፥ የነፃ ምርጫ ውጤት አስቀድሞ ስለማይታወቅ፥ መሸነፍ ብቻ ሳይሆን፥ የማሸነፍ ዕድልም ይኖራቸዋል። ዶክተር ዐቢይ ቃሉን ከጠበቀ በነፃ ምርጫ የመመረጥ ዕድል አለው።

ተወዳዳሪዎቹስ እነማን ይሆናሉ? ይኸንን የዶክተር ዐቢይ ካቢኔ ሊያስተካክለው ይችላል። ካሁን በፊት የተወዳደሩ ፓርቲዎች ወያኔዎች ቢያዳክሟቸውም አሁንም አሉ። ፓርቲን በጎሳና በሃይማኖት ላይ ማድረግ ቢከለከል ይመረጣል። ቢፈቀድም፥ ወያኔ ከቀጠቀጠው ከአማራና ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት በቀር ማንም አያሸንፍም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ግን፥ ከአንገፈገፈው የጎሳ ፖለቲካ ተላቅቆ፥ ራእዩ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያሳድግና ሕዝቡን ከረኀብ አለንጋ የሚያላቅቅ የሆነ ፓርቲ እንዲያሸንፍ ነው።

ኢትዮጵያ፡ የፍሬ፡ ዛፍ፡ የሞላባት፡ የምድር፡ ገነት፡ ናት። ሕዝቧ፥ አዳምና ሔዋን፥ ከገነት፡ ዛፎች፡ እንዳይበሉ፡ ስለታዘዙ፡ በረኀብ፡ እያለቁ ነው። ዐቢይ፡ እግዚአ፡ ብሔር፡ ትእዛዙን፡ እንዲያነሣልን፡ እንጸልይ።